OFFICE OF ARTS & CULTURE
CITY OF SEATTLE

# ለክስተቶች እና ኤግዚቢሽኖች ማመልከቻ መመሪያዎች፣ ARTS በኪንግ መንገድ ጣቢያ (ARTS at King Street Station)

## የማመልከቻ አጠቃላይ እይታ

ARTS በኪንግ መንገድ ጣቢያ በሲያትል እምብርት ውስጥ ለኪነ ጥበብ እና ባህል ለውጥ ፈጣሪ ቦታ ነው። በ2025 የቀን መቁጠሪያ ወቅት፣ 7,500 ካሬ ጫማ ስፋት ያለው የባህል ቦታ በኪንግ መንገድ ጣቢያዎች ላይ በሚደረጉ ኤግዚቢሽኖችን እና ዝግጅቶች ሃሳብ እንዲያቀርቡ እንጋብዝዎታለን። በሚታዩ የኪነ ጥበብ ኤግዚቢሽኖች፣ በትርኢቶች፣ ንባቦች፣ ትምህርቶችን በመስጠት፣ ማጣሪያዎች፣ በንባብ ቡድኖች፣ ክርክሮች፣ ንድፎች መቅረጽ እና ስዕል በመሳል፣ በእነዚህ ቅርጸቶች ጥምረት እና በሌሎችም ሀሳብ ማቅረብ ይችላሉ።

ለመረጃ፣ ለማመልከቻው ብቁነት ወይም ለመስመር ላይ ቴክኒካል ድጋፍ እርዳታ ለማግኘት፣ **ጀምስ ኮሊ (James Coley)**፣ የኪንግ መንገድ ጣቢያ ፕሮግራም መሪ፣ በ **(206) 684-4186** ወይም James.Coley@seattle.gov ይናገኙ። **የአሜሪካ የምልክት ቋንቋን (በቪዲዮ በኩል) ጨምሮ በእርስዎ ቋንቋ ሊያናግሩዎት የሚችሉ አስተርጓሚዎች አሉን።** ብቻ ይደውሉልን እና እርስዎ የሚናገሩትን ቋንቋ ይንገሩን። ጥሪውን ለመቀላቀል አስተርጓሚ እስከምናገኝ ለአጭር ጊዜ እንደሚያስጠብቅዎ ይገንዘቡ።

## ማመልከቻ

በ Submittable በኩል በመስመር ላይ ያመልክቱ። ለማመልከት ነፃ ነው። ኮምፒውተር የማግኘት ወይም የኢንተርኔት አገልግሎት ከሌለዎት፣ **James Coleyን** በ **(206) 684-4186** ወይም James.Coley@seattle.gov በተቻለ ፍጥነት ይገናኙ።

## የማብቂያ ዕለተ ቀን

የጥሪ መስመሩ ከተንከባላይ የማብቂያ ዕለተ ቀን ጋር ዘልቆ እስከ 2024 ድረስ ክፍት ሆኖ የሚቆይ ነው። በ2024 ውስጥ ለሚገመገሙ ዑደቶች እነዚህ የማብቂያ ዕለተ ቀናት አላቸው: **ሰኔ 25**፣ **መስከረም 10**፣ እና **ህዳር 9።** በእያንዳንዱ የማብቂያው ዕለተ ቀን ከምሽቱ 5 ሰዓት (ፓሲፊክ) በኋላ የሚቀርቡ ማመልከቻዎች ለሚከተለው ዑደት ታሳቢ ይደረጋሉ።

## ብቁነት

በሚከተሉት ሁኔታዎች እንደ ግለሰብ ወይም እንደ ሰዎች ቡድን ማመልከት ይችላሉ:-

- ዕድሜዎ 15 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ።
- እርስዎ ብቅ የሚሉ እና/ወይም የተመሰረቱ አርቲስቶችን ይወክላሉ።

ቡድኖች እና ድርጅቶች እንዲሁ ማመልከት ይችላሉ:-

- እነሱም ለትርፍ ያልተቋቋሙ፣ ከመሠረቱ ህዝባዊ ወይም የንግድ ድርጅቶች ሊሆኑ ይችላሉ።
- ኪነ ጥበብ እና ባህልን ለሚያካትተው ፕሮጀክት ወይም ክስተት ድጋፍ የሚፈልጉ።
- እነርሱም ለኪነ ጥበብ እና ለባህል ተልእኮ የተሰጡ/ ተግባር መሆን አይጠበቅባቸውም።
- እነርሱ ለትርፍ ያልተቋቋመ የ501(c)(3) አቋም እንዲኖራቸው አይጠበቅባቸውም።

የእርስዎ ሀሳብ አቅርቦት የሚከተሉትን ማሟላት አለበት:

- በ ARTS በኪንግ መንገድ ጣቢያ፣ 303 S. Jackson Street ቦታ ላይ መከናወን ይኖርበታል። አብዛኛው የተመረጡ ፕሮግራሞች መከናወን ያለባቸው ከላይኛው ፎቅ ላይ ነው።
- ለዘር እና ለማህበራዊ ፍትህ ካለን ቁርጠኝነት ጋር መጣጣም አለበት።
- ጠቃሚ የጥበብ እና የባህል አካል ያለው።
- ነፃ የሆነ፣ ሁሉንም እድሜ የሚያስተናግድ እና ለህዝብ ክፍት የሚሆን።
- በእኛ አዳራሽ የህዝባዊ ሰአታት ውስጥ የሚካሄድ: ከእሮብ – ቅዳሜ ከጥዋት 11፡00 ሰዓት – ምሽቱ 5፡00 ድረስ፤ የመጀመሪያ ሐሙስ ከጥዋት 11:00 - ምሽቱ 8:00 **እሁዶች እና ሰኞዎች ለክስተቶች አይገኙም።**

የእርስዎ ፕሮጀክት የሚከተሉትን ማድረግ የለበትም:-

- ምንም እንኳን ከARTS በኪንግ መንገድ ጣቢያ ውጭ ገዥዎች ለሽያጭ መታወቂያ እና የመገኛ/ የመገናኛ መረጃ ደርድረው ቢያስቀምጡም፣ የሽቀጣ ሽቀጥ ቁሳቁሶችን በቀጥታ መሸጥ ወይም ዋጋዎችን መለጠፍ ያስፈልጋል።
- የቲኬት ሽያጮችን ይጠቀሙ። ፕሮግራሞች ሁሉም በነጻ ለህዝብ መቅረብ አለባቸው።
- ለትርፍ ወይም ለንግድ ጉብኝት ክስተት የሆነ።

## የድጋፍ ገንዘብ

በገንዘብ የተደገፉ የሃሳቦች ማቅረብ በአይነት (የማዕከለ ስዕሉን ከዋና እና የግንኙነት ድጋፎች ጋር መጠቀም) ወይም የገንዘብ ድጋፍ በሚከተለው የተወሰነ መጠን መቀበል:-

- ኤግዚቢሽኖች/ የሚገቡ ሥራዎች: በአይነት ብቻ፣ $500 ዶላር፣ $1,000 ዶላር፣ $2,500 ዶላር፣ $5,000 ዶላር፣ $7,000 ዶላር
- ዝግጅቶች፡ በአይነት ብቻ፣ $500 ዶላር፣ $1,000 ዶላር፣ $2,500 ዶላር፣ $5,000 ዶላር
- እርስዎ ከጠየቁት የድጋፍ ገንዘብ ደረጃ የተለየ ሊቀርብልዎ መቻል።

እርስዎ ቀጥተኛ የፕሮጀክት ወጪዎችን የሚደግፍ የድጋፍ ገንዘብን መጠቀም ይችላሉ። የድጋፍ ገንዘብ ለመሳሪያ ግዢ ጥቅም ላይ መዋል አይችልም።

## የመረጃ አውደ ጥናቶች

ስለዚህ የገንዘብ ስጦታ እና የእርስዎን ከሁሉ ምርጥ የሆነ ማመልከቻ እንዴት ማስገባት እንደሚችሉ የበለጠ ይወቁ። ትርጓሜ ከፈለጉ፣ እባክዎትን **ጀምስ ኮሊን (James Coley)** በ **(206) 684-4186** ወይም James.Coley@seattle.gov ያግኙ።

**ምናባዊ አውደ ጥናት 1**
እሮብ፣ ሰኔ 5፣ ከ3 - 4:30 ከሰዓት በኋላ (ፓስፊክ)
ለአውደ ጥናት 1 እባክዎን ምላሽ ይስጡ

**ምናባዊ አውደ ጥናት 2**
እሮብ፣ ነሐሴ 14፣ ከ5 - 6፡30 ከምሽቱ
ለአውደ ጥናት 2 እባክዎን ምላሽ ይስጡ

**ምናባዊ አውደ ጥናት 3**
እሮብ፣ ኦክቶበር 23፣ ከ5 - 6፡30 ከምሽቱ
ለአውደ ጥናት 3 እባክዎን ምላሽ ይስጡ